በፍትሕ ዘርፍ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ግምገማዊ ጥናት ሪፖርት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሚያዚያ 2015

<u>አዲስ አበባ</u>

ማውጫ

		ገፅ
ክፍል አንድ	መግቢያ	
1.1.	የጥናቱ ዳራ	
1.2.	የዘርፉ ተቋማት ሥልጣንና ተግባራት	
1.3.	የጥናቱ ዓላማ	
ክፍል ሁለት	በፍትሕ ዘርፍ የሙስና ስጋት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ	
ክፍል ሶስት	የጥናቱ ስነ-ዘዴ	
3.1.	የጥናቱ ወሰን	
3.2.	የዝግጅት ምዕራፍ	
3.3.	የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች	
3.4.	የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ	
3.5.	የጥናቱ ተግዳሮቶች	
3.6.	የጥናቱ ውስንነቶች	
ክፍል አራት	ዘርፍ-ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና	
4.1.	የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት	
4.2.	ተጠያቂነትን ማስፈን	
4.3.	የተቋማት ግልጽነት	
4.4.	አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ	
4.5.	የንብረት አስተዳደር	
4.6.	የግዥ አስተዳደር	
4.7.	የሰው ሃብት አስተዳደር	
4.8.	የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ	
4.9.	የፕሮጀክቶች አስተዳደር	
4.10.	ኦዲትና ቁጥጥር	
4.11.	የተቋማት የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና	
ክፍል አምስት	ምክረ-ሀሳቦች	
	ማጣቀሻ ፅሁፎች	

ክፍል አንድ፡- መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study)

ሙስና የአንድን አገር መልካም አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ እድገት እና የሰብአዊ መብት መከበር በከፍተኛ ሁኔታ ከሚጎዱ ችግሮች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ሙስና ማለት ባለስልጣኖች/ሀላፊዎች ከህብረተሰቡ የተሰጣቸውን አደራ ለግል መበልጸጊያ የማዋል ብልሹ አሰራር ማለት ነው። ሐቀኝነትን የማጉደል ወይም ሕገወጥ ባህሪ ማለት ነው፡፡ ሙስና የህግ የበላይነትን በማጣመም እና ለኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ የሆነውን ተቋማዊ መሰረት በማቀጨጭ ልማትን ያዳክማል፣ ለማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ማነቆ ይሆናል፣ በመሰረተ ልማት፣ በተቋማት እና በማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ኢንቨስትመንቶችን በማዳከም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ምህዳርን ያጎለብታል፡፡ የሞራል እሴቶች ማሽቆልቆል እና ህገ-መንግስታዊ ተቋማትን እና ስልጣንን አለማክበር የሙስና መገለጫዎች ናቸዉ፡፡

ሙስናን በብቃት እና በተፈለገው ሁኔታ ለመከላከል፤ አገሮች ፣ ዘርፎች ወይም ተቋማት ለሙስና የተጋለጡበትን ስጋቶች መረዳትን ይጠይቃል፡፡ ውጤታማ የሙስና መከላከያ ዘዴዎችን ለመንደፍ እና ለመተግበር መሰረቱ የሙስና ስጋቶችን መገምገም ሲሆን ይህም ተገቢውን የአደጋ መከላከያ እርምጃዎችን ለመለየት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመምረጥ ያስችላል፡፡ እንደዚህ አይነት እርምጃዎች የመንግስት እና/ወይም የግሉ ሴክተር ድርጅቶች ጥረታቸውን እና ሀብታቸውን በጣም አንገብጋቢ እና ተፅእኖ በሚፈጥሩ የትኩረት ቦታዎች ላይ እንዲያውሉ ያስችላቸዋል፡፡

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለበርካታ ዓመታት ህጎችን በማውጣት እና በመተግበር ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ተግባራት ውስጥም ጥናትና ምርምር በማድረግ ሙስናን መከላከል አንዱ ነው፡፡ በኮሚሽኑ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ግን ለሙስና ስጋት የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ አደረጃጀቶችና አሰራሮችን በመለየት ወቅታዊ መፍትሔ የመስጠት ሥራ ትኩረት ተሰጥቶ ባለመሰራቱ፣ ሙስና በየጊዜው እየተከሰተ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር እየሆነ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ኮሚሽኑ ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ሥራን በተቋም ደረጃ የሚከታተሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አደራጅቶ ወደ ተግባር ቢገባም፣ እስካሁን በተቋማቱ ውስጥ የሙስና መከላከል ተግባራት የተገኘዉ ዉጤት በሚጠበቀው ደረጃ ላይ ደርሶ አልተገኘም፡፡

በተለያዩ ዘርፎች ስር በሚገኙ ተቋማት ሊከሰቱ ለሚችሉት የሙስና ዓይነቶች ፣ የህጎች መላላት፣ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአስተዳደር ሥርዓት፣ ደካማ ተቋማዊ ባህል፣ ደካማ የአሰራር ስርዓት፣ የግለሰቦች የሥነምግባር ጉድለት፣ የሥራ አካባቢዎች አለመመቸት እና አግባብነት የሌላቸው የሥራ ግንኙነቶች፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራረብ፣ አያያዝ እና አፈታት ግልፅነት አለመኖር፣ የመረጃ አያያዝ ደካማነት ፣ ወዘተ እንደ ተቋማዊ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህና የመሳሰሉት ክስተቶች በተለያዩ ዘርፎች ስር ባሉ ተቋማት ላይ የሚያስከትሉትን የሙስና ተጋላጭነት አደጋ በሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት መመርመር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡

በመሆኑም ይህን የሙስና ሥጋት ችግር በዘላቂነት ለመቀነስ ሲባል በፍትሕ ዘርፍ ስር ባሉ ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሆኑ ጉዳዮችን ሙያዊና ስልታዊ የሆነ የተቋማት የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ የሙስና መከላከያ ምክረ-ሀሳቦችን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

1.2. የዘርፉ ተቋማት ሥልጣንና ተግባራት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 40 መሰረት የፍትሕ ሚኒስቴር የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ያውላል፡፡ ይህ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለፍትሕ ዘርፍ (ለፍትሕ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት) ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች እርስ በርሳቸው ባልተግባቡበት የፍትሐ-ብሔር ጉዳይ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣
- በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር የሚገኙ ከወንጀል ጋር የተገናኙ ንብረቶች የማስመለስ ሥራዎችን ይሠራል፣ ያስተባብራል፤
- በፌደራል ፖሊስ ምርመራ ዘርፍ የሚከናወኑ የምርመራ ሥራዎችን ይመራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤
- በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 እና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን አዋጅ ቁጥር 551/1999 የተመለከቱት የዳኝነት አካላት በሥሩ ሆነው በአዋጆቹ የተመለከቱትን ከዳኝነትና ችሎት ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎችን ሥራ ላይ ያውላል፤
- ታረሚዎችን የማረምና ማነፅ ሥራዎችን፣ በዘርፉ የሚደረጉ ጥናቶችንና የሚሰጡ ሥልጠናዎችን፣ ከግብር ጋር የተያያዙ የይግባኝ ሥራዎችን፣ የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ሥራዎችን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የሚመለከቱ ሥራዎችን ያስተባብራል፣
- የወንጀል ጉዳዮች ዐቃቤያነ-ሕግ ዘርፍ የአሠራር ነፃነቱ ተጠብቆ በተለይም የወንጀል ክስ፣ የክርክርና የፍርድ ማስፈጸም ሥራዎች ለማከናወን የሚያስችል አደረጃጀትና አሠራር ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፣

1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

አጠቃላይ ዓላማ፡-

የፍትሕ ዘርፍ ተቋማትን የአሰራር ስርዓት ከሙስና ስጋት አንፃር በመገምገም የሙስና ተጋላጭነት ትንተና ማካሄድ ነው፡፡

ንዑስ አላማዎች፡-

የፍትሕ ዘርፍ ተቋማትን፥

- የአሠራር ስርዓቶች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣
- የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማስቀመጥ፣

ክፍል ሁለት፦ በፍትሕ ዘርፍ የሙስና ስጋት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ

ሙስና በተለምዶ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ወይም በአደራ የተሰጠን ሥልጣን ለግል ጥቅም ማዋል ተብሎ ይተረጎማል:: ይህም ማለት ተገቢ ያልሆነ የፍትሕ አገልግሎት አሰጣጥ እና የዜጎች የህግ ከለላ ማጣት ነው:: ሙስና የፍትሕ ገለልተኝነትን ሊጎዱ የሚችሉ ሁሉንም አይነት ተገቢ ያልሆኑ ተጽእኖዎችን ያጠቃልላል፤ በፍትሕ ስርዓቱ ውስጥ ያሉ ተዋናዮችን ጨምሮ የህግ ባለሙያዎችን እና የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪዎችን ያካትታል::

ለማንኛውም የፀረ-ሙስና ትግል ስኬት ትልቅ እንቅፋት የሚሆነው በፍትሕ ተቋማት ያለው የሙስና እና የብልሹ አሰራር ስርዓት ነው:: በፍትሕ ስርዓቱ ውስጥ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ከመድረሱ በፊት በብልሹ አሰራር ውስጥ ሊሳተፉ የሚችሉ በርካታ ተቋማት አሉ:: እነዚህም የፖሊስ ሃይል፣ ጠበቆች እና አቃቤ ህጎችን ያካትታሉ:: ሙስና በሚፈጸምበት ጊዜ በተለያዩ አካላት መካከል ያለውን ትስስር ማወቅ አስፈላጊ ነው::

ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል (Transparency International, 2007) በፍትሕ ስርዓቱ ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን የሚያስከትሉ በርካታ ምክንያቶችን ለይቷል:: ከነዚህም መካከል፡- ዝቅተኛ የሆነ የዳኞች እና የፍርድ ቤት ሰራተኞች ደሞዝ፣ ደካማ ስልጠና እና የሥነምግባር ጉድለት፣ በፍርድ ቤቶች ውስጥ ግልጽነት ማጣት ሙስና እንዲፈጠር ያደርጋል (Noel Pepys, 2007፣ USAID, 2009):: በፍርድ ቤቶች ውስጥ የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎችን ለመመርመር የሚረዱ ዘዴዎች ግልጽነት የጎደላቸው ናቸው:: ለምሳሌ በሜክሲኮ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ዳኞችን የመቆጣጠር እና የመቀጣጫ ዘዴዎች ግልጽ ያልሆኑ ሲሆኑ ምርመራዎችን የማካሄድ ኃላፊነት ያለው አካል ግን ሙሉ በሙሉ ነፃ አይደለም (Carbonell, 2007):: በአፍጋኒስታን ውስጥ የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስርዓቱ ውስጥ ያሉ የተበላሹ ጉዳዮችን ለመለየት፣ ለመመርመር እና ለፍርድ ለማቅረብ ምንም አይነት ውጤታማ ዘዴ እንዳልነበረው አረጋግጧል (Chêne, 2007)::

በፍትሕ አካላት ውስጥ ከሚታዩ የሙስና ዓይነቶች አንዱ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት እና የመንግስት ስልጣን መያዝ ነው:: እንደ ሩሲያ እና አርጀንቲና ባሉ አንዳንድ አገሮች በዳኝነት ላይ ያለው የፖለቲካ ተጽእኖ እየጨመረ ነው (Transparency International, 2007):: የፖለቲካ ጣልቃገብነት የፍትሕ ስርዓቱን ከፍተኛ የሆነ ተጽእኖ በማሳደር ሙስና እና ብልሹ አሰራር እንዲኖር ያደርጋል (Buscaglia, 2007)::

በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ፍርድ ቤቶች ብዙ ጊዜ ለሰዎች ለመድረስ አስቸጋሪ ናቸው (DFID, 2000)፡፡ ሙስና ይህንን ሁኔታ ሊያባብሰው ይችላል፣ የስርዓቱን ተደራሽነት፣ ጥራት እና ህጋዊነት የበለጠ ይቀንሳል፡፡

በተለያዩ ሀገራት ውስጥ ያሉ የውስጥ ደንቦች እና አግባብነት ያላቸው ዓለም አቀፍ ሰነዶች ሙስናን ለመቋቋም የተለያዩ የግዴታ ማዕቀፎችን ያዘጋጃሉ፡፡ ነገር ግን የፍትሕ ስርዓቶች ራሳቸው የሙስና እና የተደራጁ ወንጀሎች ኢላማ ሆነው ይታያሉ፡፡ በወንጀል ፍትሕ ሰንሰለት አንድ ደረጃ ላይ የተፈጸመ የሙሰና ድርጊት አጠቃላይ ሂደቱን በእጅጉ የሚጎዳ እና አልፎ ተርፎም ህብረተሰቡ በህግ እና በስርአት ላይ ያለውን እምነት ሊሸረሽር ይችላል፡፡ በፍርድ ቤት ሂደቶች ውስጥ መብቶችን በመጠየቅ እና ውሎችን ለማስፈጸም የሚገጥሙ ተግዳሮቶች ህጋዊ አለመተማመንን ይፈጥራሉ፡፡ በመጨረሻም ንግድን፣ የስራ ፈጠራ መንፈስን እና ኢንቨስትመንትን ያዳክማል፡፡

በፍትሕ ዘርፍ የሚሰሩ ሰዎች የገንዘብ ጉቦ ወይም ውለታ ሲሰጡ የክስ መዝገቦችን እና ማስረጃዎችን አልፎ ተርፎም ተጠርጣሪዎችን በማጥፋት፣ ጉዳዩን በማዘግየት፣ አጠራጣሪ የቅጣት ውሳኔዎችን በመስጠት ወይም እስረኞችን አድሎአዊ በሆነ መንገድ በመያዝ ህብረተሰቡ በፍትሕ ተቋማት ላይ እምነት እንዲሸረሸር ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ዜጎች ግጭቶችን ለመፍታት እና መብቶቻቸውን ለማስከበር በአማፂያን ወይም አሸባሪዎች እና መሰል መዋቅሮች ወደሚመሩ መደበኛ ያልሆነ የፍትሕ ዘዴዎች ሊዞሩ ይችላሉ፡፡

በፍትሕ ዘርፍ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር መንስኤ ተደርገው ከሚወሰዱት ችግሮች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡-

- በመርማሪዎች፣ በዐቃብያነ-ሕግ፣ በዳኞች እና በምስክሮች መካከል ትክክለኛ ቅንጅት አለመኖር፣
- ቁልፍ ተዋናዮች (ህግ አስከባሪዎች፣ ዳኞች እና አቃብያነ-ህጎች) በየራሳቸው ሥራ አፈፃፀም ቴክኒካዊ ብቃት ማጣት፣
- በጉዳዮች አያያዝ ላይ አላስፈላጊ መዘግየትን የሚያስከትሉ ጊዜ ያለፈባቸው የአሰራር ደንቦች፣
- ውጤታማ የማህበረሰብ-አቀፍ መረጃ እና የትምህርት ፕሮግራሞች እና ተግባራት አለመኖር፣
- የፍትሕ አካላትን (ህግ አስከባሪዎችን፣ አቃብያነ-ህጎችን፣ ዳኞችን እና ሌሎች ተዛማጅ ሰራተኞችን) በፓርቲ/ፖለቲካ ተሳትፎ መሾም፣
- ለፍርድ ቤት ሰራተኞች፣ ለህግ አስከባሪዎች፣ ለአቃብያነ-ህጎች እና ለህዝብ ተወካዮች መጠነኛ የበጀት ድልድል፣
- በምርመራ እና በማስረጃ አያያዝ ላይ የሚሰጠው ስልጠና በቂ አለመሆን፣
- በቅድመ ወይም መደበኛ ምርመራ ወቅት ምስክሮች አለመቅረብ፣
- የፖሊስ መኮንኖች ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር ለማዋል አለመቻል (ብዙ ጊዜ የፖሊስ መኮንኖች ብዙ ሙከራዎች ቢያደርጉም ተከሳሹን በተጠቀሰው አድራሻ ማግኘት ባለመቻላቸው የእስር ማዘዣው ሊቀርብ እንደማይችል በመግለጽ ምላሽ ይሰጣሉ)፣
- የፖሊስ ምስክሮች መገኘት እና ፍርድ ቤት በሚቀርቡበት ጊዜ ዝግጁ አለመሆን፣
- ምስክሮች በሚመሰክሩበት ጊዜ የመግባቢያ ችሎታ ማነስ፣

ክፍል ሶስት፡- የጥናቱ ስነ-ዘዴ

3.1. የጥናቱ ወሰን (Scope of the study)

ይህ ጥናት የተካሄደው በፌደራል የፍትሕ ሚኒስቴር እና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተጠሪ በሆኑት በሚከተሉት አምስት ተቋማት ላይ ነው፡-

- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን፣
- የፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን፣
- የፌደራል ፍትሕና ህግ ኢንስቲትዩት፣
- የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት፣
- የፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ፣

3.2. የዝግጅት ምዕራፍ

በመጀመሪያ ለሙስና ሥጋት ሊሆኑ የሚችሉ 10 የትኩረት ርእሰ-ጉዳዮችን በመለየት የመረጃ መሰብሰቢያ ቼክ-ሊስት ተዘጋጅቷል፡፡ እነዚህ 10 ርእሰ-ጉዳዮች ማንኛውም የመንግስት ተቋም ሊተገብራቸው የሚገቡና ተመሳሳይ ባሕሪ ያላቸው አሰራሮች ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው ተቋማት ከተቋቋሙበት ዐላማ አንፃር የራሳቸው የሆነ ልዩ ባሕሪ አላቸው፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ ከተቋማቱ ልዩ ባሕሪ ሊመነጩ የሚችሉና የመለያየት ሁኔታ የሚስተዋልባቸውን የሙስና ስጋቶች ለመለየት አንድ ተጨማሪ ርእሰ-ጉዳይ ተካቷል፡፡

በመቀጠልም በተዘጋጀው ቼክ-ሊስት ዙርያ ለጥናት ቡድን አባላት (መረጃ ሰብሳቢዎች) ስልጠና በመስጠት ወደ መረጃ መሰብሰብ ስራ ተገብቷል፡፡ የተሰጡት ስልጠናዎች ተጨባጭ የሠነድ ፍተሻ በማደረግ መረጃዎችን እንዴት መሰብሰብ እንደሚቻል ለጥናት ቡድን አባላት ግንዛቤ ፈጥረዋል፡፡

3.3. የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ቼክ-ሊስት (የዳሰሳ መጠይቅ) እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች (brainstorming) ናቸው፡፡ ከየተቋማቱ የተሰበሰቡ የተለያዩ ሰነዶች ለሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ቼክ-ሊስት፡- የጥናት ቡድን አባላት የተቋማት የተለያዩ የሥራ ክፍል ኃላፊዎችንና ሰራተኞችን በማወያየት እንዲሁም (እንዳስፈላጊነቱ) በምልከታ የተዘጋጀውን ቼክ-ሊስት እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ይህን ጥናት ከሌሎች ለየት የሚያደርገው በቼክ-ሊስት ላይ የተነሱ ነጥቦች አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጣቸው በሰነድ ወይም በምልከታ ሲረጋገጡ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የሙስና ግንዛቤ (perception) ጥናት ሳይሆን በተጨባጭ መረጃ የተቋማት የስራ አፈፃፀም ግምገማ ላይ የተሞረኮዘ የሙስና ተጋላጭነት ጥናት ነው፡፡

ሰነዶች፡- የተቋማቱ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ የውስጥና የውጪ ኦዲት ሪፖርቶች፣ ዓመታዊ በጀት ዕቅድ፣ የግዥ አፈጻጸም፣ ዓመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የሙስና

መከላከል ሠነዶች፣ የጥቆማ ሪፖርት አያያዝ፣ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሪፖርቶች፣ ወዘተ ተዳሰዋል፡ ፡

የሃሳብ ማጎልበቻ ዉይይት፡- ከ10ሩ ርዕሰ-ጉዳዮች ጋር ታያያዥነት ያላቸውን ወይም በቀጥታ በቼክ-ሊስት ውስጥ ያላተካተቱትን የሙስና ስጋቶች በጥቂቱ ለመዳሰስ የበርካታ አመታት ዕውቀት ካላቸው በጥንቃቄ ከተመረጡ ሃላፊዎች እና ባለሙያዎች (experts) ጋር ሃሳብ የማጎልበት ውይይት ተካሂዷል።

3.4. የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ

የዚህ ጥናት አቀራረብ በአብዛኛው ዓይነታዊ (qualitative) ነው። ገላጭ ትንተና (descriptive analysis) አሀዛዊ መረጃዎችን (የፕሮጀክቶች የወጪ መረጃና አፈፃፀም፣ የግዥ አፈፃፀም ማሳያዎች፣ የውጭ እና የውስጥ የኦዲት ሪፖርት ግኝቶች፣ ወዘተ) ለመተንተን ሥራ ላይ ውሏል። ከተለያዩ ምንጮች (ቼክ-ሊስት፣ ሰነዶች እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች) የተሰበሰቡ ዓይነታዊ መረጃዎችን ለመተንተን ይህ ጥናት በሰፊው ተቀባይነት ያለውን የጭብጥ ትንተና (thematic analysis) ተጠቅሟል። በዳሰሳ ጥናቱ ቡድን መሪዎች አስተባባሪነት የጥናት ቡድን አባላት ከየተቋማቱ የተሰበሰቡትን ጥሬ መረጃዎች በዘርፍ ደረጃ በማጠቃለል ትንተና አካሂደዋል። የጥናቱ አማካሪዎች በበኩላቸው የሙስና ስጋቶችን በመለየትና በመተንተን ዘርፍ-ተኮር የሙስና መከላከል ምክረ-ሀሳቦችን አስቀምጠዋል።

3.5. የጥናቱ ተግዳሮቶች (Challenges of the study)

ጥናቱ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግዳሮቶች አጋጥመውታል፡-

- የተቋማት ኃላፊዎች/ሰራተኞች በተያዘላቸው ቀጠሮ ያለመገኘትና ጥናቱን የሚያከናውኑትን ባለሞያዎች የማመላለስ፤
- የተቋማት ኃላፊዎች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣

3.6. የጥናቱ ውስንነቶች (Limitations of the study)

ይህ የዳሰሳ ጥናት ቀድሞ በተመረጡና ለሁሉም ተቋማት ተመሳሳይ በሆኑ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ በማተኮር የተሰራ ከመሆኑ አንፃር የዘርፉን የሙስና ስጋቶች ሙሉ ለሙሉ ለይቷል ለማለት አያስደፍርም። በሌላ አገላለፅ በዚህ ጥናት ያልተለዩ ሌሎች የሙስና ስጋቶች በዘርፉ ውስጥ እንዳሉ ይታመናል። ሆኖም ግን በቀጣይ ለሚሰሩ ጥልቅ ጥናቶች እንደ መንደርደሪያ ሆኖ እንደሚያገለግል መናገር ይቻላል።

ክፍል አራት፡- ዘርፍ-ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና

የፍትሕ ዘርፍ የስራ አፈጻጸም እና የሙስና ስጋት ግምገማዊ ትንተና በ11 ርዕሰ-ጉዳዮች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1. የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት

የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የቅንነት፣ ታማኝነት፣ ገለልተኝነት፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ዋና እሴቶች ላይ የተመሰረተ ሥነምግባራዊ ድርጅታዊ ባህልን ለማጎልበት ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ክፍሎቹ ከተሰጣቸው ኃላፊነቶች መካከል፣ የክልል እና የፌደራል ህጎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የተቋሙን የሥነምግባር ፖሊሲዎች መገምገም እና ማዘመን፣ በተቋሙ ውስጥ ካሉ የሥነምግባር ጉዳዮች ጋር በተያያዙ የህግ መስፈርቶች ላይ ከፍተኛ አመራሮችን ማማከር፣ ለአመራር እና ሰራተኞች በሥነምግባር ደረጃዎች (ethical standards) ላይ የሥልጠና ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት እና መተግበር እንዲሁም የሰራተኞች የሥነምግባር ጉድለትን በተመለከተ የሚነሱ ቅሬታዎችን መገምገም እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን መምከር ይገኙበታል፡፡ የሥነምግባር ክፍሎች እነዚህን ኃላፊነቶች ለመወጣት በሰው ኃይል፣ በበጀት፣ በቁሳቁስ፣ ወዘተ መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ የዘርፉ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አደረጃጀት እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

በፍትሕ ዘርፍ ስር ከሚገኙት ተቋማት ውስጥ ገሚሶቹ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸውን በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት ያቋቋሙ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ግን ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በወሰነው አደረጃጀት መሰረት ክፍሉን አዋቅረዋል፡፡ በተጨማሪም ከአንድ ተቋም በስተቀር በሌሎቹ ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የስራ መደቦች በሰው ኃይል እንዳልተሟሉ ከቅጥር ደብዳቤዎች እና ከስራ ክፍል ምልከታ ለማወቅ ተችሏል (በክፍሉ ውስጥ አንድ ሰራተኛ ብቻ ተመድቦ የሚሰራበት እንዲሁም ከ75% በላይ የሚሆኑት የክፍሉ የስራ መደቦች በሰው ሃይል ያልተሸፈኑበት ተቋማት አሉ)፡፡ በሁለት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አመታዊ ዕቅድ እንዳላቸው የሚገልፅ መረጃ አልቀረበም፡፡ ምቹ የስራ ቦታ ከመፍጠር አንፃር፣ ከአንድ ተቋም በስተቀር የቀሩት በዘርፉ ስር የሚገኙ ተቋማት ለሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ሚሟላታቸው በበጎ ጎን የሚታይ ነው፡፡ በጀትን በሚመለከት እንደሌሎች የስራ ክፍሎች የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን በሚጠይቁበት ወቅት የሚፈቀድበት አሰራር (ፑል ሲስተም) ከሞላ ጎደል በሁሉም ተቋማት እየተተገበረ እንደሆነ ታውቋል፡፡

በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ከሥነምግባር መከታተያ ክፍል በተጨማሪ የሃብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤ የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ የግዢ ኮሚቴ፣ የደረጃ እድገት ኮሚቴ፣ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ ሆኖም ግን በሁለት ተቋማት ውስጥ የህግ ክፍል የለም፡፡

በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ ዘዴ ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለው በአካል በመገኘት ጥቆማ የሚሰጥበት የሃሳብ መስጫ ሳጥን ነው፡፡ ኢ-ሜይል፣ ድረ-ገጽ እና ስልክ (hotline) የመሳሰሉት ዘመናዊና ተደራሽ የጥቆማ መስጫ መንገዶች የተተገበሩት በግማሾቹ የዘርፉ ተቋማት ብቻ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተለይ በአንዱ ተቋም ምንም አይነት የሙስናና ብልሹ አሠራር ጥቆማ መቀበያ አሠራር ስርአት አለመዘርጋቱ በስራ ቦታ ምልከታ ተረጋግጧል፡፡

በፍትሕ ዘርፍ ስር ከሚገኙት ተቋማት ገሚሶቹ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው ከሌሎች ክፍሎች (ከህግ ክፍል፣ ተቋማዊ ለውጥ፣ ውስጥ ኦዲት፣ ወዘተ) ጋር በቅንጅት እንደሚሰሩ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ የሕግና ሌሎች የስራ ድጋፎችን ከተቋማዊ ለውጥ እንዲሁም ከህግ ክፍል ከመሳሰሉት በሚጠይቁበት ጊዜ በቀና መንፈስ እንደሚያገኙም ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ እንዲሁም የብልሹ አሰራር ምልክት በሚኖርበት ጊዜ ተገቢነት ካላቸው የስራ ክፍሎች ጋር በጋራ የሚሰሩ ሲሆን በአንዳንድ ኮሚቴዎች ውስጥ ተወካይ በመሳተፍ የማጣራት ስራዎች ይሰራሉ፡፡ በተቀሩት ተቋማት ግን ቅንጅታዊ አሰራር ስለመኖሩ ምንም መረጃ የለም፡፡

የሕግ ክፍል ራሱን ችሎ በተቋቋመባቸው ተቋማት ውስጥ ውጫዊ እና ውስጣዊ ውሎች ላይ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ እንደሚያደርግ እንዲሁም ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት አሠራር ስርዓት እንዳለ ከሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዘርፉ ስር ካሉት ተቋማት በአንዱ ግን ይህ አሰራር አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- በሁሉም የዘርፉ ተቋማት በሚባል ደረጃ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የስራ መደቦች በሰው ኃይል አልተሟሉም፣ እንዲሁም በተወሰኑ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አመታዊ ዕቅድ እንዳላቸው የሚገልፅ መረጃ አልቀረበም፡፡ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 እና አዋጁን ተከትሎ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን የወጣው መመርያ ቁጥር 20/2013 የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋሞቻቸው የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎችን በባለቤትነት የሚያስተባብሩ የሥራ ክፍሎች ሆነው እንደሚደራጁ ይገልጻል፡፡ ሆኖም ግን ከላይ የተገለፁት ጉድለቶች በዘርፉ ስር የሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ይህን ተልዕኮ ለመወጣት ብቁ ቁመና ላይ አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡
- በተወሰኑ ተቋማት ውስጥ የህግ ክፍል አለመኖሩ ታውቋል፡፡ ይህ የሆነው ከተቋማቱ ልዩ ባህርይ አንፃር ሊሆን ቢችልም፣ ብልሹ አሰራሮች ሲከሰቱ አጣርቶ ተጠርጣሪዎችን ለህግ የሚያቀርብ እና ተዛማች ስራዎችን የሚሰራ ራሱን የቻለ የህግ ክፍል አለመኖሩ ለሙስና በር ሊከፍት ይችላል፡፡
- በጥናቱ መሰረት ዘመናዊና ተደራሽ የጥቆማ መስጫ መንገዶች የተተገበሩት በግማሾቹ የዘርፉ ተቋማት ብቻ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ጥቆማ የተከሰቱ የሙስና ድርጊቶች እና ብልሹ ተግባራትን ለመለየት፣ ለማጣራት እና ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ አይነተኛ የትግል መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም የጥቆማ አቀባበል ስርአት አለመዘርጋት እንዲሁም ተደራሽ አለማድረግ በዘርፉ ውስጥ ከፍተኛ የሙስና ስጋት ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡
- በገሚሱ የዘርፉ ተቋማት ውስጥ ከሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ስለመኖሩ ምንም መረጃ የለም፡፡ ይህ ግኝት ቅንጅታዊ አሰራር መደበኛ እና የተዋቀረ (structured) የሙስናና ብልሹ አሰራር መረጃ ልውውጥ ለማድረግ እንዲሁም የጋራ ትንተና ለማካሄድ ካለው ፋይዳ አንፃር የዘርፉ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን አለማድረጋቸውን አመላካች ነው፡፡

4.2. ተጠያቂነትን ማስፈን

ለዜጎች ፍትሕን ለማረጋገጥ፣ አስተዳደራዊ በደልን ለማረምና ለመቀነስ፣ የመንግስት በጀትና ሃብት በአግባቡ ስራ ላይ ውሎ የዜጎች ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ለማስቻል፣ የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክሲያዊ መብቶች እንዲጠበቁ እንዲሁም በሥነምግባር የታነፀ ሙስናን የሚጸየፍ ዜጋን ለማፍራት የፍትሕ ተቋማትን ተጠያቂነት ማስፈን ሚናው በጣም ወሳኝ ነው፡፡ የተጠያቂነት ስርአት የተቋማት ሀላፊዎች እና ሰራተኞች ለድርጊታቸው፣ ለባህሪያቸው፣ ለአፈፃፀማቸው እና ለሚወስዷቸው ውሳኔዎች ኃላፊነት የሚወስዱበት የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው፡፡ የዚህ ስርአት በአግባቡ ተግባር ላይ መዋል ማንኛውም አመራር/ሰራተኛ ከተሰጠው ስልጣንና ከተጣለበት ኃላፊነት አንፃር በአፈፃፀሙ፣ በውሳኔውና በሚያስከትላቸው ተፅዕኖዎች እንደሚገመገም እንዲሁም ብልሹ አሰራሮች መኖራቸው ከተረጋገጠ አንደአስፈላጊነቱ የእርምት እርምጃዎች እንደሚወሰዱ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ተጠያቂነትን ከማስፈን ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡ ፡

የፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነት ባህሪይ ያላቸው ክፍሎች ላይ ጥናት አከናውኖ የአሰራር ማሻሻያዎች ማድረጉን፣ እንዲሁም የፌደራል ፍትሕና ህግ ኢንስቲትዩት በተሽከርካሪና ነዳጅ አጠቃቀም ዙርያ ጥናት በማካሄድ ብክነትን ለመከላከል የሚያስችሉ አሰራሮች ለመዘርጋት ጥረት ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ቀሪዎቹ የዘርፉ ተቋማት ግን ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎችን አሰራር በተመለከተ የሙስና ስጋት ጥናት ስለማከናወናቸውም ሆነ የማሻሻያ እርምጃዎች ስለመውሰዳቸው የሰነድ ማስረጃ ለማግኘት አልተቻለም፡፡ በገሚሱ የዘርፉ ተቋማት የደንበኞች እርካታ በየጊዜው በገለልተኛ አካል የሚጠና መሆኑ ቢገለጽም ይህን የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

ተጠያቂነት ለማስፈን ከሚያስችሉ ተግባራት መካከል የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) ማዘጋጀትና መተግበር አንዱ ነው፡፡ ይህን ኃላፊነት ከመወጣት አንፃር በዘርፉ ስር የሚገኙ አብዛኛው ተቋማት የሥነምግባር ደንብ ማዘጋጀታቸውን ከሰነድ ማስረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን ደንቡ በሰራተኛው ዘንድ ተግባራዊ መደረጉን የሚያመላክቱ መረጃዎች አልተገኙም፡፡ የተወሰኑ ተቋማት የደንቡን ረቂቅ በማዘጋጀት ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

በገሚሱ የዘርፉ ተቋማት ውስጥ የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ የተደረጉ ቅድመ-መከላከል ስራዎች እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን የስፖርት ክፍል ከአልባሳት ግዢ ጋር በተገናኘ በደረሰ ጥቆማ ማጣራት ተካሂዶ በኃላፊዎችና ባለሙያዎች ላይ እርምጃ ለማስወሰድ በሂደት ላይ መሆኑን፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን የሥነምግባር ክፍል ቅሬታን መሰረት አድርጎ የጨረታ ሂደትን ለማራዘም የውሳኔ ሀሳብ ማቅረቡን፣ እንዲሁም የፌደራል ፍትሕና ህግ ኢንስቲትዩት ከስልጠና አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የቀረበን ጥቆማ በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ ማቅረቡን የተሰበሰቡ ማስረጃዎች አመልክተዋል፡፡ በተቀሩት ተቋማት ግን ጥቆማ ደርሶ የተደረጉ ቅድመ-መከላከል ስራዎች ስለመኖራቸው መረጃ አልቀረበም፡፡

በግማሹ የዘርፉ ተቋማት ውስጥ በሥነምግባር ጉድለት ምክንያት በአመራሩም ሆነ በፈጻሚ አካላት ላይ ምንም ዓይነት የቀረቡ ክሶች እንደሌሉ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተቀሩት ሶስቱ ተቋማት ግን የቀረቡ ክሶች እንደነበሩና አብዛኛዎቹ ክሶች ውሳኔ የተሰጣቸው መሆኑን ከሰነድ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዘርፉ ስር የሚገኙ የአራት ተቋማት የህግ ክፍሎች በፍትሀ-ብሔር እና በወንጀል ጉዳዮች ባለፉት ሁለት ዓመታት ክሶች እንደመሰረቱና ውሳኔ ከተሰጠባቸው ክሶች አብዛኛዎቹን እንዳሸነፉ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን በተወሰኑ ተቋማት ላይ የህግ ክፍሉ አሸናፊ መሆኑን የሚገልጽ የፍርድ ቤት ውሳኔ ሰነድ አልተገኘም፡፡ በዘርፉ ቀላል የማይባሉ ኬዞች እንዳሉ እና በሂደት ላይ እንደሆኑ እንዲሁም የጊዜ ቀጠሮ ጉዳይ ትኩረት የሚፈልግ መሆኑን ጥናቱ ያመላክታል፡፡

በዘርፉ ስር በሚገኙ አራት ተቋማት ውስጥ ባለፉት ሁለት ዓመታት ቅሬታዎች እንደቀረቡ የተገለጸ ሲሆን በቀሩት ሁለት ተቋማት ግን ምንም ዓይነት ቅሬታዎች እንዳልቀረቡ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በእነዚህ አራት ተቋማት ውስጥ በአጠቃላይ 348 ቅሬታዎች ቀርበው በ301 (86.5%) ላይ ውሳኔ መተላለፉን ከሰነዶች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለፀረ-ሙስና ትግል የአመራር ሚና ወሳኝ መሆኑን የተለያዩ የጥናት ውጤቶች ያመለክታሉ፡፡ ነገር ግን በፍትሕ ዘርፍ ስር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት በሚያስብል ደረጃ የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ ክንውን በተቋማቱ የበላይ አመራሮች ክትትልና ግምገማ እንደሚደረግበት የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ በተወሰኑ ተቋማት ውስጥ የሥነምግባር ክፍል የስራ አፈጻጸም ግምገማ እንደማንኛውም የስራ ክፍል ግምገማ ሲካሄድ አብሮ የሚገመገም መሆኑ ቢገለጽም ይህን የሚያመላክት ሰነድ/ቃለ-ጉባኤ አልተገኘም፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- የተቋማቱ የህግ ክፍሎች በፍትሀ-ብሔር እና በወንጀል ጉዳዮች ላይ ከመሰረቷቸው ክሶች ውስጥ ቀላል የማይባሉ ኬዞች የውሳኔ ሂደት በእንጥልጥል ላይ እንደሚገኝ መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ ተደጋጋሚ የችሎት ቀጠሮ (adjournments)፣ የግብዓት እጥረት፣ ገለልተኛ ውሳኔ ለመወሰን የዳኞች ፍርሀት፣ ጊዜ ያለፈባቸው ህጎች እና ስርዓቱን ለማሻሻል የፖለቲካ ቁርጠኝነት ማነስ የዳኝነት ሥርዓቱን እንደሚያንትተው ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ የዘገየ የፍትሕ አሰጣጥ ስርዓት በበኩሉ ሙስናን በተለያዩ መንገዶች ይወልዳል፡፡ ስለዚህም የዘርፉ ተቋማት ይህን ክፍተት ቢያንስ ለመቀነስ አበክረው ሊሰሩ ይገባል፡፡
- በዘርፉ ስር የሚገኙ ገሚሱ ተቋማት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎች አሰራር ላይ የሙስና ስጋት ጥናት አለማካሄዳቸው ታውቋል፡፡ እንዲሁም ሁሉም ተቋማት በሚያስብል ደረጃ የደንበኞች እርካታን በየጊዜው በገለልተኛ አካል ስለማስጠናታቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ እነኚህ ተግባራት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጡ የሚችሉ አሰራሮችን በጥናት በመለየት ቅድመ-መከላከል ስትራተጂዎችን ለመቅረፅ እንዲሁም ተጠያቂነትን ለማስፈን ካላቸው ፋይዳ አንፃር ተቋማቱ የሚጠበቅባቸውን አለማድረጋቸውን ያሳያል፡፡
- በዘርፉ ስር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ የተደረጉ ቅድመ-መከላከል ስራዎችን የሚያሳይ መረጃ አላቀረቡም፡፡ በመሆኑም የሙስና ስጋቶች አድገው ወደ ሙስና ከመሸጋገራቸው በፊት በመረጃዎች ላይ በመመስረት የሚወሰድ የእርምት እርምጃ አለመኖር ለሃብት ብክነትና ለደንበኞች እንግልት ሊዳርግ ይችላል፡፡

4.3. የተቋማት ግልፅነት

የመንግስት ተቋማት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ግልፅነትን ሊላበሱ ይገባል፡፡ ግልፅነት ዜጎች ለህብረተሰቡ አገልገሎት ለመስጠት የተዋቀሩ ተቋማትን የስራ አፈፃፀም እንዲሁም የሚከሰቱ ችግሮችን መንስኤ እና መዘዞችን በተመለከተ በቂ መረጃ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው፡፡ የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖሊሲዎች እና የውጤቶች አተገባበር መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያጠቃለለ ነው፡፡ ግልፅነት የጎደለው አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ምንም እንኳን መልካም ውጤት ቢመዘገብም የተአማኒነት እና ቅቡልነት ጥያቄ ሊነሳበት ስለሚችል የሚያሳድረው ተፅእኖ ቀላል አይደለም፡፡ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለውን የግልፅነት ስራዎች በዚህ ክፍል ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ተቋማዊ ግልፅነት ለማስፈን እንዲያግዝ የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ከመረጃ ስብሰባው ሂደትና መስክ ምልከታው መረዳት ይቻላል፡፡ በዘርፉ ስር ያሉ የሁሉም ተቋማት ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ከሠራተኞችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበት ወደ ተግባር እየተገባ መሆኑን ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም የዕቅድና በጀት ትግበራው የተሳካ እንዲሆን አጋዥ ሚናውን ይጫወታል ተብሎ ይታመናል፡፡ የተቋማት ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ እንደሚደረጉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተጨማሪም በአራቱ የዘርፉ ተቋማት በስራ ሂደቶች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚመለከታቸው አካላት እንደሚሳተፉ በጥናቱ ወቅት ከተሰበሰበ መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በቀሪዎቹ ሁለቱ ተቋማት ግን ይህ ስለመደረጉ መረጃ አልቀረበም፡፡ በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት ውሳኔዎች (በተለይም ለህዝብ ይፋ መደረግ ያለባቸው) በመገናኛ ብዙኃን እና በማህበራዊ ሚዲያ በተከታታይ ተደራሽ እንደሚደረጉ ታውቋል፡፡

በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት አምስቱ የግዥና ጨረታ ማስታወቂያ በይፋ በጋዜጣ እንደሚያሰራጩ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ግን የግዥና ጨረታ ማስታወቂያዎችን ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ስለማድረጉ መረጃ አልቀረበም፡፡ አራቱ የዘርፉ ተቋማቱ ለሚዲያ፣ ለምርመራ ጋዜጠኞች እና ሌሎች አካላት መረጃዎችን ስለመስጠታቸው አመላካች መረጃዎች የቀረቡ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ሁለቱ ግን መረጃዎችን ከመስጠት አንጻር ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት መረጃ የሚያሰራጩበት ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ድረ-ገጽ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- የሚመለከታቸው አካላትን በስራ ሂደቶች ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ለማሳተፍ አለመቻል በውሳኔዎች ተአማኒነት ላይ ጥያቄ የሚያስነሳ ከመሆኑም ባሻገር ግልፅነትን ከማስፈን አኳያ በዘርፉ ውስጥ ክፍተቶች እንዳሉ አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡
- አንዱ የዘርፉ ተቋም የግዥና ጨረታ ማስታወቂያዎችን በይፋ እንደሚያሰራጭ የሚያመላክት መረጃ አልተገኘም፡፡ ይህ የግልፅነት ክፍተት በእርግጥ ተከስቶ ከሆነ ለሁሉም

የምርት/አገልግሎት አቅራቢዎች እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ ከመንፈጉ በተጨማሪ ለጥቅም ግጭት ስለሚዳርግ ከፍተኛ የሙስና ስጋት ነው፡፡

- የተወሰኑት የዘርፉ ተቋማት ለሚዲያ፣ ለምርመራ ጋዜጠኞች እና ሌሎች አካላት መረጃዎችን ስለመስጠታቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ሚዲያ (በተለይም የምርመራ ጋዜጠኝነት) ሙስናን ለህዝብ እይታ በማጋለጥ እንዲሁም ያለምንም ተጠያቂነት (with impunity) የሚፈፀሙ ጎጂ ስራዎችን በመዋጋት ረገድ ከሚጫወተው ወሳኝ ሚና አንፃር የመገናኛ ብዙሃን ተደራሽ አለመሆን የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

4.4. አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

ሙስናን ለመዋጋት ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የህግ የበላይነት ከማስፈን ባሻገር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸው መርሆች በመደንገግ ፈፃሚዎች ስራቸውን ህግ በተከተለ መሰረት እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታቸውን ይፈጥራል፡፡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው መሻሻል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ከአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ተያይዘው የተሰሩ ስራዎችን ከዚህ በታች ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በጥናቶች እና በዕለት-ተለት ስራዎች ከሚመነጩ መረጃዎች በመንተራስ አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ በተቋማቱ እየተሰራ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለዚህም አመላካች የሚሆነው ሁሉም ተቋማት በሚባል ደረጃ የሥነምግባር ደንቦችና ሙስና መከላከል የሚያስችሉ መመሪያዎች በማውጣት ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆናቸው ነው፡፡ ከዚሁ በተጓዳኝ ህጎችን በፍትሕ ሚኒስቴር የማስመዝገብ ልምዱም እየዳበረ መሆኑን ከተገኙት መረጃዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ፀድቀው የሚወጡ መመሪያዎችና ደንቦች ለተገልጋዮች/ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ በማድረግ ረገድ በተለይም በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እየሰሩ መሆናቸውን ከአራቱ የዘርፉ ተቋማት የተሰበሰቡ መረጃዎችና ምልከታዎች ያሳያሉ፡፡ በፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ፀድቀው የሚወጡ መመሪያዎች በቀላሉ ተደራሽ ስለመሆናቸው አመላካች የሆኑ ሰነዶች ያልቀረቡ ሲሆን፣ በፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ደግሞ በየማረሚያ ማዕከሎች ቤተ-መጽሃፍት እንደሚገኙ ታውቋል፡፡

በዘርፉ ስር ካሉ ተቋማት አራቱ ለአመራሮች እና ሰራተኞች በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች አተገባበር ላይ ስልጠና እየሰጡ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህን የሚያመላክት መረጃ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን እና ከፌደራል ፍትሕና ህግ ኢንስቲትዩት ማግኘት ግን አልተቻለም፡፡

በአራት የዘርፉ ተቋማት የዜጎች ቻርተር መዘጋጀቱ በመረጃ ሲረጋገጥ፣ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት እና በፍትሕ ሚኒስቴር ግን ቻርተሩ እንደተዘጋጀ ቢገለጽም ይህንን የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በሁሉም የዘርፉ ተቋማት በሚባል ደረጃ የዜጎች ቻርተር ለተገልጋዮች ተደራሽነቱ እጅግ ውስን ነው፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- በተወሰኑ የዘርፉ ተቋማት ውስጥ ለአመራርና ሰራተኞች በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ አተገባበር ላይ ስልጠና ስለመሰጠቱ መረጃ አልቀረበም። ይህ ጉድለት በሠራተኞች የሥራ አፈፃፀም ላይ ከሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ በተጨማሪ ሠራተኞች ከዕውቀት ክፍተት ጋር ተያይዞ ለብልሹ አሠራር እንዲጋለጡ ሊያደርግ ይችላል።
- በተወሰኑ የዘርፉ ተቋማት የዜጎች ቻርተር ስለመዘጋጀቱ መረጃ አልቀረበም። እንዲሁም በአብዛኛው ተቋማት የተዘጋጀው ቻርተር በተገቢው መንገድ ለተገልጋዮች ተደራሽ አልተደረገም። ይህ ክፍተት ተገልጋዮች ባለማወቅ መብታቸውን በገንዘብ እንዲገዙ እንዲሁም የተቋማቱ አሠራር ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዳይኖረው ሊያደርግ ስለሚችል የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

4.5. የንብረት አስተዳደር

የንብረት አስተዳደር ስርአት ውጤታማነት የሚለካው ከንብረት ርክክብ እስከ ማስወገድ ድረስ በየደረጃው የሚከናወኑ ተግባራትን በአግባቡ በመተግበር ንብረቱ በአግባቡ ተጠብቆ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ሲቻል ነው። ንብረትን ከማስተዳደር አኳያ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የተገዙ ንብረቶችን መረከብ፣ በተገቢው መንገድ ማከማቸትና መጠበቅ፣ ለተጠቃሚዎች ማድረስና ንብረቶቹ ለተገቢው አገልግሎት መዋላቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ያለአገልግሎት የተቀመጡትን (ወይም የአገልግሎት ጊዜያቸውን ያጨረሱትን) የንብረት አስተዳደር መመሪያን በተከተለ መልኩ ማስወገድ ዋናዎቹ ናቸው። በተጨማሪም በየጊዜው የንብረት ቆጠራ በማካሄድ የማረጋገጥ ስራ መስራት ያስፈልጋል። ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ካለው የንብረት አስተዳደር ስርአት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን ለመተንተን ተሞክሯል።

የቀረቡት ሰነዶች በተቋማቱ መደበኛ የንብረት ቆጠራ ስራ እየተሰራ መሆኑን የሚያመላክቱ ናቸው። በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ በአውቶሜሽን የተደገፈ መሆኑን ለመመልከትም ተችሏል። በተጨማሪም የተገዙ እቃዎች የግዢ መመሪያ ሥርዓት የተከተሉና በሠነድ እየተመዘገቡ መረጃዎች በአግባቡ እንዲደራጁ ከማድረግ አንፃር የተሰራው ስራም በጥሩ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን በዘርፉ ስር ባሉ ተቋማት የተደረጉት የሰነድ ፍተሻዎች ያሳያሉ። ሆኖም ግን ከንብረት አያያዝ ጋር የሚጠቀሰው ጉዳይ የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርዓት በዘርፉ ተቋማት ውስጥ አለመተግበሩ ነው።

በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት ውስጥ የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝራቸው ቀርቦ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተገምግመው የሚወገዱ መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ። ንብረቶቹም በሽያጭ፣ በስጦታ እና በድጋፍ መልክ በሚመለከተው አካል ፀድቆ የማስወገድ ስራ ተሰርቷል። በፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ግን በየባለሙያው እጅ የሚወገድ ንብረት እያለ በ2013 እና በ2014 በጀት አመት ምንም አይነት የንብረት ማስወገድ ስራ አልተሰራም። በአምስቱ የዘርፉ ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶች ከመወገዳቸው በፊት አስቀድሞ በተዘጋጀ ስቶር ተገቢ ጥበቃ እና አያያዝ የሚደረግላቸው መሆኑን

የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል፡፡ በፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ግን የሚወገዱ ንብረቶች ስቶር ባለመኖሩ በየቢሮው አመቺ ባለሆነ መንገድ ተነጠባጥበው እንዳሉ ለማየት ተችሏል፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርዓትን አንዳቸውም የዘርፉ ተቋማት እንዳልተገበሩ በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ ስርአት አለመተግበሩ እቃዎች በበቂ መጠን በመጋዘን ባሉበት ሁኔታ ተጨማሪ ግዥዎችን በማከናወን የህዝብን ሃብት ለብልሽት እና ብክነት ሊዳርግ ይችላል፡ ፡
- መወገድ ያለባቸውን ንብረቶች በንብረት ማስወገድ መመሪያ መሰረት አለማስወገድ ያለምንም ጥቅም የተቀመጡ ንብረቶችን ድጋፍ የሚሹ ወገኖች/ተቋማት ሊጠቀሙበት የሚችሉበትን ዕድል ወይም መንግስት ሊያገኝ ይችል የነበረውን ገቢ የሚያሳጣ ትልቅ ክፍተት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

4.6. የግዥ አስተዳደር

ተቋማት ሥራቸውን በሚፈለገው ጊዜና ጥራት ለማከናወን አስፈላጊ የሚባሉ ግብአቶችንና የስራ መሳሪያዎችን ሟሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህን ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የዕቃና የአገልግሎት ግብአቶችና መሳሪያዎች ለሟሟላት የግዥ ስርአትን የተከተለ ስልታዊ አካሄድ ይጠይቃል፡፡ የግዥ ስርአቱ ያለበትን ደረጃ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናቱ እንደሚከተለው ተንትኗል፡፡

ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት በዘርፉ ስር ባሉ የተወሰኑ ተቋማት የግዥ ስርአትና አፈፃፀምን በተመለከተ የተሟላ መረጃ የሚሰጥ ኃላፊ ማግኘት በተለያዩ ምክንያቶች አስቸጋሪ ነበር (የሚመለከታቸው አካላት መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ ያልሆኑበት ተቋምም ታይቷል)፡፡ በዘርፉ ስር ያሉ አብዛኛው ተቋማት ግዥ የሚከናወነው በእቅድ፣ ከየክፍሉ ያለ ፍላጎትን መሰረት በማድረግ እንዲሁም ስቶክ ላይ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ ስለመሆኑ በተደረገ ውይይት ግንዛቤ መወሰዱ ቢገለፅም ሒደቱን የሚያሳይ መረጃ ግን አልተገኘም፡፡

ከግዥ በፊት የገበያ ጥናትን በተመለከተ አብዛኛው በዘርፉ ስር ያሉ ተቋማት በተጠናከረ መልኩ እንደማያከናውኑ እንዲሁም የገበያ ጥናት አድራጊ ኮሚቴም አለማደራጀታቸውን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ዉስን ተቋማት ጥናት እንደሚያካሂዱ የገለፁ ቢሆንም የገበያ ጥናት ማካሄዳቸዉን የሚያመላክት ማስረጃ ማግኘት ግን አልተቻለም፡፡ በአንድ ተቋም ሪፖርት ላይ ግን የገበያው አለመረጋጋትና የአቅራቢዎች የመንግስት ግዥ ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት እየቀነሰ መምጣት ከግዥ በፊት ባለው የገበያ ጥናትና በአጠቃላይ ግዥ ሂደት ላይ ክፍተት እየፈጠረ መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ግዥ የሚከናወነው በግዢ ኤጀንሲ በማዕቀፍ ስለሆነና የግዥ ትዕዛዝ የሚሰጠው ኤጀንሲው በመሆኑ የገበያ ጥናት ትርጉም የሌለው መሆኑ በአንድ ተቋም ተገልጿል፡፡በዘርፉ ስር ባሉ ተቋማት የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት ግምገማ መሰረት ያለዕቅድ ግዢዎች ቁጥራቸው ከፍተኛ ሲሆን፣ የቀጥታ ግዢዎችና ለአንድ አቅራቢ በተደጋጋሚ የሚሰጡ ግዢዎችም እንደተስተዋሉ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ብዙ የአፍሪካና በዓለም ላይ ያሉ አገሮች የግዥ ሥርዓታቸውን ለማሻሻል የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥን (EGP - Electronic Government Procurement) በመሳሪያነት ይጠቀማሉ፡፡ የፌዴራል መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የተመረጡ ተቋማት EGPን እንዲተገብሩ በያዘው አቅጣጫ መሰረት በዘርፉ ስር ባሉ መስሪያ ቤቶች የአተገባበር ስራዉ በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ የኤሌክትሮኒክ ግዥ መፈፀሚያ ሲስተሙ ተዘጋጅቶ የተላከባቸው፣ በ2016 በጀት ዓመት ለመጀመር ያቀዱና የግዢ ሥርዓት ተዘጋጅቶ ፀድቆ ወደ ሥራ እንዲገባ የተደረገባቸው ተቋማት ይገኛሉ፡፡ ተቋማት የEGP ስርአትን ተግባራዊ ለማድረግ የሄዱበት ርቀት የሚያበረታታ ነው፡፡

በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት ውስጥ ቅሬታ የቀረበባቸው እንዲሁም የሙስና ጥርጣሬ ቀርቦባቸው የተሰረዙ ግዥዎች አለመኖራቸው ታውቋል፡፡ ይህ በጎ ልምድ ሊበረታታና ሊቀጥል ይገባዋል፡፡ ከግዢ ኤጀንሲ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ የማዕቀፍ ግዢ የሚወስደው ጊዜ በእቃዎች አቅርቦት ላይ የሚያስከትለው መዘግየትና ተቋማት ጥራት ያለው ማቴሪያል ያለማግኘት ጉዳይ እንደችግር ተነስተዋል፡፡ እነኚህም የድርጅቶች የስራ ቅልጥፍና ላይ ተጽእኖ ስላላቸው የግዢ ኤጀንሲ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- በሁሉም በሚያስብል የዘርፉ ተቋማት ግዥ የሚከናወነው ከየክፍሉ ያለ ፍላጎትን መሰረት በማድረግ እንዲሁም ስቶክ ውስጥ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ ስለመሆኑ መረጃ አልቀረበም፡፡ ይህ ክፍተት በቂ ስቶክ ባለበት ሁኔታ ተጨማሪ ግዥዎችን በማከናወን የህዝብን ሃብት ለብልሽት እና ብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- በዘርፉ ተቋማት በርካታ ከዕቅድ ውጭ፣ የቀጥታና ከአንድ አቅራቢ ተደጋጋሚ ግዥዎች መኖር የዘርፉ የግዥ ስርዓት የሙስና ስጋት እንዳለበት አመላካች ናቸው (እነኚህ ግዢዎች እንዲካሄዱ የሚያስገድድ ገፊ ምክንያት (ህጋዊ መሰረት) ሊኖር የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ)፡፡
- አብዛኛው ተቋማት የገበያ ጥናት አድራጊ ኮሚቴ አለማደራጀታቸውና ግዥ ሲከናወን በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ ለተጋነነ የምርቶች/አገልግሎቶች ዋጋ ስለሚጋብዝ የሙስና ስጋት ነው፡፡

4.7. የሰው ሃብት አስተዳደር

የአንድን ተቋም ስኬት ከሚወስኑ መስረታዊ ግብኣቶች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ያላቸው የሰው ሃብት ነው፡፡ ስኬት የሚረጋገጠው የሰው ሃብት በአግባቡ ማስተዳደር ሲቻል ነው፡፡ ለዚህ የሚያግዙ አሰራሮችና መዋቅሮች መዘርጋት ተገቢነቱ የጎላ ነው፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የሰው ሃብት አስተዳደር ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዘርፉ ውስጥ ያሉት ተቋማት የቅጥር፣ የዝውውር፣ የቅሬታ ሰሚ/ዲሲፒሊን ኮሚቴ በማቋቋም ስራ እየሰሩ መሆኑን ከተቋማት የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሰያሉ፡፡ ለምሳሌ በዘርፉ ስር ባሉት ተቋማት በአጠቃላይ 190 ቅሬታዎች ቀርበው 161ቱ ውሳኔ አግኝተዋል፡፡ አፈፃፀሙም በመቶኛ ሲሰላ 85 ፐርሰንት ይሆናል፡፡ ከዚህም በመነሳት በዘርፉ ቅሬታዎችን በማስተናገድ እና መፍትሔ በመስጠት

በኩል አመርቂ ሊባል የሚችል ስራ መሰራቱን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሰራተኛ ቅጥር ለመፈፀም ተቋማቱ ማስታወቂያዎችን በጋዜጣ ወይም በመገናኛ ብዙሀን የማስተዋወቅ ስራ እየሰሩ ነው፡፡ የሰራተኞች ቅጥር፣ ምደባና ዕድገት በውድድር ላይ የተመሰረተ እና ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ መሰረት እየተካሄደ መሆኑን ከሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን የፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለአስተዳደር ሰራተኞች ከተፈቀደው የስራ መደብ የተሸፈነው ሲሶው ብቻ መሆኑን ያሳያል፡፡

በተቋማቱ ሃሰተኛ የሰራተኛ የትምህርት ማስረጃና ስራ ልምድ ሰነድ የማጣራት ስራ ከአንድ ተቋም ጅምር ስራዎች በስተቀር ያልተከናወነ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ በመንግስት በኩል ከ2012 ዓ.ም በፊት የማጣራት ስራ እንዲከናወን አቅጣጫ ቢቀመጥም ከሦስት አመት በኋላም ቢሆን ተግባራዊ አለመሆኑ ታይቷል፡፡ በገሚሱ የዘርፉ ተቋማት ውስጥ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ (Automated) የሰው ሃብት መረጃ ስርዓት የማደራጀት ስራዎች እንደተሰሩ ከቃለ-ጉባኤ እና ከተተገበሩ ሲስተሞች ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተቀሩት ተቋማት ግን ይህ ስርአት አልተተገበረም፡፡ በተጨማሪም አንድ ተቋም ብቻ የተቀናጀ የሰው ሃብት መረጃ አያያዝ ሥርዓት (Integrated Civil Service Management Information system (ICSMIS)) በማበልፀግ ስራ ላይ አውሏል፡፡ ስልጠናን በተመለከተ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው ከአንድ የዘርፉ ተቋም በስተቀር ሌሎቹ በሥነምግባር ዙሪያ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- ለሰራተኞች ከተፈቀደው የስራ መደብ የተሸፈነው ጥቂት ብቻ መሆኑ የስራ መደራረብ ወይም ጫና በመፍጠር በአፈፃፀም ላይ አሉታዎ ተፅእኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ሙስናን ከውስጥ መከላከል የሚቻለው አመራርና ሰራተኞች የታማኝነት፣ የተጠያቂነት፣ የፍትሃዊነት እና የመተማመን ጠንካራ የሞራል እሴቶችን ካዳበሩ ነው፡፡ የሥነምግባር ስልጠናዎች በዚህ ረገድ ያላቸው አስተዋፆ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት በሥነምግባር ዙሪያ የስልጠናዎች አለመኖር አመራርና ሰራተኞች ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዲፀየፉና እንዲታገሉ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት በሚፈለገው ልክ ከግብ እንዳይደርስ ሊያደርግ የሚችል ክፍተት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡
- በዘርፉ ተቋማት ሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ የማጣራት ስራ አለመሰራቱ ያለበቂ ችሎታ እና የስራ ልምድ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ሊኖሩ የሚችሉበትን ክፍተት በመፍጠር የመንግስት ሃብት ያላግባብ ጉዳት እንዲደርስበት እንዲሁም ጥራት ለጎደለው የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ሊዳርግ ይችላል፡፡
- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የሰው ሃብት አስተዳደር ስርአት በገሚሱ የዘርፉ ተቋማት አለመገንባቱ በቅጥር፣ ዝውውር፣ እድገት፣ ወዘተ ውሳኔዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡

4.8. የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ

የአገሪቱ የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ ህግ በሚደነግገው መሰረት የፈደራል ተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች ሀብታቸውን የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው፡፡ ተቋማትም ቅጥር ከመፈፀማቸው በፊት የመጀመሪያ ወይም ዳግም ምዝገባ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት በዘርፉ ተቋማት ውስጥ የሃብት ምዝገባ ማድረግ የሚገባቸው አመራሮች ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ሀብታቸውን አሳውቀዋል፡፡ ሰራተኞችን በተመለከተ ግን ሙሉ ለሙሉ ምዝገባ ያከናወኑት ገሚሶቹ የዘርፉ ተቋማት ብቻ ናቸው፡፡ በተለይ በሁለት ተቋማት ውስጥ የምዝገባ ምጣኔው ከ40 በመቶ የዘለለ እንዳልሆነ የተሰበሰቡ መረጃዎች አሳይተዋል፡፡

በተወሰኑ ተቋማት ውስጥ የሃብት መረጃው ዲጂታላይዝድ ሲስተም ስርዓት ውስጥ እንዲገባ መደረጉን መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ የኢንተርኔት መቆራረጥና የሰራተኛው በሲስተም የመጠቀም ልምድ አናሳ መሆን ዲጂታላይዝድ የሃብት ማሳወቅና ማስመዝገብ ስራን እያጓተተ እንደሆነ ተቋማቱ ገልፀዋል፡፡

የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ ሥርዓት የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል እንዲሁም ምንጫቸው ያልታወቀ ንብረቶችን ለመለየት ካለው ፋይዳ አንፃር በዘርፉ ተቋማት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ አለመደረጉ እንደስጋት ምንጭ ሊወሰድ ይችላል፡፡

4.9. የፕሮጀክቶች አስተዳደር

ፕሮጀክቶች ከቅድመ ግንባታ እስከ ፍፃሜቸው ድረስ አግባብነት ያላቸውን ህጎችና መስፈርቶች ተከትለው እየተፈጸሙ ስለመሆናቸው ቴክኒካል ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርግ የተለየ የኦዲት መዋቅር ባለመኖሩ፣ በተለያዩ አካላት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ለጥራት መጓደልና ብክነት እየተጋለጡ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክትን በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ፣ በጀትና የጥራት ደረጃ ለማጠናቀቅ የዲዛይን ጥራት፣ የጨረታ አወጣጥ ሂደት፣ የክፍያ ስርአት፣ የኮንትራት አስተዳደር እና ከመሰል ጉዳዮች ጋር ተያይዞ የተጠናከረ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ያፈልጋል፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የግንባታ ፕሮጀክት አስተዳደር ለሙስና ያለውን ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በፍትሕ ዘርፍ ስር የሚገኙ አራት ተቋማት ምንም አይነት ፕሮጀክት እንዳላልነበራቸው (እንደሌላቸው) ታውቋል፡፡ ከተቀሩት ሁለት ተቋማት ያለፉት አምስት ዓመታት የፕሮጀክት አፈፃፀም ሪፖርቶች እንዲሁም ከአማካሪዎችና ከተቋራጭ ደብዳቤዎች የሚከተሉትን መረዳት ተችሏል፡-

- ተጀምረው በጊዜያቸው ያላለቁ 74 ፕሮጀክቶች (ግምታቸው ብር 26,334,789,632.32)፣
- የዋጋ ማስተካከያ የተደረገባቸው 48 ፕሮጀክቶች (የ44ቱ ፕሮጀክቶች የገንዘብ መጠን ብር 248,688,990.96 ሲሆን የአራቱ የዋጋ ማስተካከያ የገንዘብ መጠን አልተቀመጠም)፣
- ተጨማሪ ስራ የተሰጠባቸው 72 ፕሮጀክቶች (ግምታቸው ብር 1,198,743,301.12)፣
- ተቋራጩ የጠፋባቸው ሶስት ፕሮጀክቶች (ግምታቸው ብር 1,296,747,295.62)፣
- ውል የተቋረጠባቸው ሶስት ፕሮጀክቶች (ግምታቸው ብር 47,844,651.00)፣
- ተቋራጩ የተከሰሰበት አንድ ፕሮጀክት (ግምቱ ብር 24,393,820.24)፣

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- ግዙፍ በጀት የፈሰሰባቸው በርካታ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያለመጠናቀቅ የሚገነቡ ፕሮጀክቶችን ፍላጎት መሠረት ያደረገ የግንባታ ዲዛይን ዝግጅት ላይ ከሚከሰቱ ክፍተቶች እንዲሁም ከፕሮጀክቶች አስተዳደር የክትትልና ቁጥጥር መላላት ሊመነጭ የሚችል አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ በተጨማሪም ያላግባብ ተጨማሪ ወጪ ለመጠየቅ ከተያዘላቸው ቀነገደብ በላይ እንዲሻገሩ ለማድረግ የታለመ ሊሆን ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው፡፡
- ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ የሚሰጥበት አሰራር (Variation work order) ምናልባት ቀድሞ የፕሮጀክቱን ዕቅድ በተገቢው መንገድ ከመገምገምና የሚሰሩ ስራዎች አስቀድመው እንዲካተቱ ከማድረግ አንፃር ክፍተት እንዳለ ጠቋሚ ነው፡፡
- የውሎች መቋረጥ እንዲሁም የተቋራጮች መጥፋት መፅደቅ የማይገባቸው ጨረታዎችን ከማፅደቅ ወይም ማሸነፍ የማይገባቸው ተጫራቾች እንዲያሸንፉ ከማደረግ ጋር ተያይዞ የመምጣት ዕድል ሊኖረው ስለሚችል አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡

4.10. ኦዲትና ቁጥጥር

ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣትና ሕጋዊና ጤናማ የሆነ የገንዘብና የንብረት አያያዝ እንደተከተሉ ለማረጋገጥ የፋይናንስና ንብረት ክንውን የውስጥ ኦዲት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡ ፡ በተጨማሪም የስራቸውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ለዚሁ ተግባር በተቋቋመ የውጭ ኦዲተር የማስገምገም ግዴታ አለባቸው፡፡ በዚሁ ዳራ የዘርፍ መስሪያ ቤቶች የኦዲት አስተዳደር ስርአት በጥናቱ የታየ ሲሆን በፍትሕ ዘርፍ ዉስጥ ባሉ ድርጅቶች ያለው አሰራር እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

በዘርፉ ስር ያሉ ተቋማት በየአመቱ የውስጥ ኦዲት ስራ እየሰሩ መሆናቸዉን ከሪፖርቶች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በየተቋማቱ ያሉ አመራሮች የውስጥና የውጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይትና ግምገማ የማካሄድ ልምድ ያላቸው መሆኑን ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ በ2014 በጀት አመትም የውስጥና የውጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ አብዛኛው ተቋማት ውይይትና ግምገማ ያካሄዱ መሆኑን የግምገማ ቃለ-ጉባኤዎች ያስረዳሉ፡፡

የውጭ ኦዲት ሪፖርትና የተደረጉ ማሻሻዎችን በተመለከተ አብዛኛው የዘርፉ ተቋማት መሻሻል እንዳለ በቃል ከመግለጽ ዉጪ ለዋና ኦዲተር የተላከውን ሪፖርትና የተወሰዱ ማስተካከያ እርምጃዎችን የሚያሳይ ሰነድ ማግኘት አልተቻለም፡፡ የ2014 በጀት አመት የውጭ ኦዲት ሪፖርትን በተመለከተም ይህ መረጃ በተሰበሰበበት ወቅት ለተቋማቱ በቅርብ ጊዜ የተላከ በመሆኑ የጥናት ቡድኑ ሊያገኘው አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት በውጭ ኦዲት ግኝት መሰረት የተሰሩ ማሻሻያዎችን መገምገም አልተቻለም፡፡ የኦዲት ሪፖርት ተደራሽነትን በተመለከተ በዘርፉ ዉስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ ተቋማት ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል ተደራሽ የሚያደርጉ ሲሆን ለሌሎች የስራ ክፍሎች ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር ልምድ አለመኖሩን ከተጻፉ ደብዳቤዎች ለማየት ተችሏል፡፡ በዘርፉ ስር ያለ አንድ ተቋም ግን ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች በሙሉ ተደራሽ ማድረጉን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህ በጎ ልምድ በተቋሙ ሊቀጥልና በዘርፉ ስር ባሉ ሌሎች ተቋማትም ሊለመድ ይገባል፡፡

የሒሳብ አያያዝ ሥርዓትን ከማሻሻል አንፃር የፋይናንስ መረጃ አስተዳደርን ሙሉ በሙሉ ወደ ተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት (IFMIS - Integrated Financial Management Information System) ለማስገባት የተደረጉ ሙከራዎች በአንዳንድ ተቋማት ታይተዋል። ይህ አዲስ አሰራር በትክክል እየተተገበረ መሆኑን በግልፅ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ግን ማግኘት አልተቻለም።

የ2013 እና 2014 በጀት ዓመት የተቋማት የኦዲት ግኝቶች መሰረት በተደጋጋሚ ከተነሱ ችግሮች መካከል፡- ያለዉድድር ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ግዥ መፈጸም፣ እንዲሁም ከተመዘገቡ አቅራቢዎች መገዛት የሚገባዉን ዕቃ በለቀማ ግዥ ዘዴ መግዛት፣ ተገቢ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ተወራርዶ መገኘት፣ መቀነስ የሚገባው ግብር (ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ) ሳይቆረጥ መገኘት፣ ስልጣን ባለዉ አካል ያልተፈቀደ ወይም ያልፀደቀ ክፍያ ተፈፅሞ መገኘት፣ እና ከስራ ለለቀቁ ሰራተኞች አላግባብ ክፍያ/ደመወዝ መክፈል ተጠቃሽ ናቸው።

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- በዘርፉ ተቋማት ተገቢ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ተወራርዶ መገኘት እንዲሁም ስልጣን ባለዉ አካል ያልተፈቀደ ወይም ያልፀደቀ ክፍያ ተፈፅሞ መገኘት የፋይናንስ መመሪያ ጥሰትን እንዲሁም የቁጥጥር ሥርዓት መላላትን አመላካች ሊሆን ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው።
- የውጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ በመመስረት የተወሰዱ ማሻሻያዎች ስለመኖራቸው የሚያሳይ መረጃ ከአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት አልቀረበም። የማሻሻያ እርምጃዎች አለመኖር የተከሰቱ ብልሹ አሰራሮች እንደገና ለተቋሙ ስጋት የመሆናቸውን አጋጣሚ ስለሚያሰፋ እንደ ትልቅ ክፍተት ሊወሰድ ይችላል።
- በዘርፉ ተቋማት የተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት ከጅምር ባለፈ በትክክል እየተተገበረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም። ይህ ሥርዓት የፋይናንስ ቁጥጥርን ውጤታማነት ለማጠናከር ካለው ፋይዳ አንፃር በተቋማቱ አለመተግበሩ እንደ ክፍተት ሊወሰድ ይችላል።

4.11. የተቋማት የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና

በፍትሕ ዘርፍ ስር በሚገኙ ተቋማት ከፍተኛ የሙስና ስጋት (ተጋላጭነት) እንዳላቸው የተገለጹ አሰራሮችና ሂደቶች (processes) እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡-

- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፍቃድ አሰጣጥ፣
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ንብረት አስተላለፍ፣
- የሰነድ ማረጋገጥ ስራ፣
- ታክስ ይግባኝ ላይ የሬጅስትራር እና የዳኝነት ስራ፣
- የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር፣
- የተሽከርካሪዎች ስምሪትና የነዳጅ አጠቃቀም፣

ክፍል አምስት፡- ምክረ-ሀሳቦች

በዚህ ውስጥ ዳሰሳና ትንተና ጥልቅ ምክረ-ሃሳብ ማቅረብ ቢያስቸግርም የሚከተሉትን ጥቅል የመፍትሄ ሃሳቦች ለማቅረብ ተሞክሯል፡-

- የሰነድ ማረጋገጥ ስራ ላይ፣ በታክስ ይግባኝ ዙሪያ የሬጅስትራር እና የዳኝነት ስራዎች ላይ፣ እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፍቃድ አሰጣጥ እና ንብረት አስተላለፍ ላይ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን በሙስና ስጋት ጥናት ለይቶ የማሻሻያ እርምጃዎችን መውሰድ የግድ ይላል፡፡
- የዘርፉ ተቋማት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና ነዳጅ አጠቃቀም ላይ በቂ የክትትልና ቁጥጥር ስርአት መገንባት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- በዘርፉ ተቋማት ውስጥ በተደጋጋሚ የዋጋ ማስተካከያ የተደረገባቸውና ተጨማሪ የስራ ውል የተሰጠባቸው በርካታ ፕሮጀክቶች መኖራቸው በጥናቱ ለማየት ተችላል፡፡ እነኚህ ፕሮጀክቶች ግዙፍ የሆነ በጀት የሚያንቀሳቅሱ ከመሆናቸው አንፃር የፕሮጀክት አስተዳደር አቅምን በማሳደግ የግንባታ ሂደት ለሙስና እና ብልሹ አሠራር እንዳይጋለጥ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡ ፡
- በዘርፉ ስር ባሉ ተቋማት ያለዕቅድ ግዢዎች፣ የቀጥታ ግዢዎችና ለአንድ አቅራቢ በተደጋጋሚ የሚሰጡ ግዢዎች እንደተስተዋሉ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እነኚህ ግዢዎች እንዲካሄዱ የሚያስገድድ ህጋዊ መሰረት ሊኖር ቢሆንም የሙስና ስጋት ስለሆኑ ግዢዎቹ ለምን በግልፅ ጨረታ እንዳልተከናወኑ፣ ሳይታቀዱ እንደተገዙና ለምን ከአንድ አቅራቢ በተደጋጋሚ እንደተገዙ አሳማኝ ምክንያቶች ሊቀመጥላቸው ይገባል፣ ዝርዝር ምክንያቶቹም ተደራሽ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡
- የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP) ስርአት ሃብትን በቁጠባ ለመጠቀምና የግዢ ሥርዓቱን በእቅድ ከመምራት አንፃር ያለውን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተቋማት የማዘመኑን ስራ በማጠናቀቅ ቀድሞ ከነበሩበት የማንዋል ሥራ ወደ ዲጂታል ሲስተም በፍጥነት እንዲዛወሩ ግፊት ያስፈልጋል፡፡
- በዘርፉ ተቋማት የተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት ከጅምር ባለፈ በትክክል እየተተገበረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ይህ ሥርዓት የሒሳብ አያያዝ እና ምዝገባን ወቅታዊና ትክክለኛ በሆነ መንገድ በማደራጀት ጥልቅ (comprehensive)፣ አስተማማኝ እና ወቅታዊ የፋይናንስ መረጃዎችን ለዋና ኦዲተር፣ ለፓርላማ፣ ለምርመራና አቃቤ ህግ አካላት በማቅረብ የፋይናንስ ቁጥጥርን ውጤታማነት ለማጠናከር ካለው ፋይዳ አንፃር ተቋማቱ በቀጣይ አትኩረው ሊሰሩበት ይገባል፡፡
- በተቋማቱ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃና ስራ ልምድ የማጣራት ስራ ያልተከናወነ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ በሃገሪቱ ከሚታየዉ የሀሰተኛ ሰነዶች ስርጭት አንፃር ተቋማቱ ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩት የሚገባ ጉዳይ መሆን ከግምት ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ ሥርዓቶች የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል፣ ምንጫቸው ያልታወቀ ንብረቶችን ለመለየት እና ሰፊ የህዝብ አገልግሎት ታማኝነትን ለመገንባት ሁለገብ መሳሪያ

ናቸው። ስለዚህም የዘርፉ ተቋማት ይህን ስርአት በአፋጣኝ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

- የወረቀት ሥራ ለተደጋጋሚ አካላዊ ግንኙነት እና ለሙስና ሊጋብዝ የሚችል በመሆኑ ዲጂታላይዝድ ሲስተሞችን መዘርጋት (የአውቶሜሽን ስራዎችን ትኩረት ሰጥቶ ማበልፀግና መተግበር) እንዲሁም ተገልጋዮች በሲስተሞች እንዲጠቀሙ የግንዛቤ ስራ መስራት ላይ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።
- ብልሹ አሰራሮች ሲከሰቱ አጣርቶ ተጠርጣሪዎችን ለህግ የሚያቀርብ፣ ለሥነምግባር ክፍሉ በሙስና ጉዳዮች ዙርያ የህግ ምክር አገልግሎት የሚሰጥ እንዲሁም ተዛማች ስራዎችን የሚሰራ ራሱን የቻለ የህግ ክፍል በየተቋማቱ ውስጥ መደራጀት ይኖርበታል።
- ተቋማት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን ለመለየትና የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድ ወቅቱን የጠበቀ የሙስና ስጋትና የደንበኞች እርካታ ጥናት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የማጣቀሻ ጽሑፎች

1. Buscaglia, E., 2007, 'Judicial corruption and the broader justice system' in Transparency International, 2007, *Global Corruption Report: Corruption in Judicial Systems*, http://www.transparency.org/publications/gcr/gcr_2007
2. Carbonell, M., 2007, 'Judicial corruption and impunity in Mexico', in Transparency International, 2007, *Global Corruption Report: Corruption in Judicial Systems*, http://www.transparency.org/publications/gcr/gcr_2007
3. Chêne, M., 2007, *Tackling Judicial Corruption in Afghanistan*, U4 Expert Answer.
4. Noel Pepys, M., 2007, 'Corruption within the judiciary: causes and remedies' in Transparency International, 2007, *Global Corruption Report: Corruption in Judicial Systems*, http://www.transparency.org/publications/gcr/gcr_2007
5. Transparency International, 2007, *Global Corruption Report: Corruption in Judicial Systems*, http://www.transparency.org/publications/gcr/gcr_2007
6. USAID, 2009, *Reducing corruption in the judiciary office of democracy and governance,* USAID program brief.